# የወያኔ ምርጫ አልተሳካም።

## ከታዴዎስ ታንቱ፣

የአካባቢና የማሟያ የሚል ቅፅል የተሰጠው የወያኔ የሥልጣን ዕድሜ ማራዘሚያ ምርጫ በመራጮች እምቢተኝነት ከትግራይ በስተቀር በተቀሩት የኢትዮጵያ ክፍላተ-ሀገር የተጠበቀውን ያህል ውጤት እንዳላመጣ ከየሥፍራው የደረሱን መረጃዎች አመለከቱ።

ቀደም ሲል የወያኔ ምርጫ ቦርድ በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ አንድ ሺህ መራጮች የምርጫ ካርድ የወሰዱ መሆኑን የገለፀ ሲሆን የምርጫው ውጤት ሲታይ ግን ተመዝግበው ካርድ ከተቀበሉ መራጮች መካከል አብዛኛው ወያኔንም ሆነ በተቃዋሚ ስም የተመዘገቡ የወያኔ አጃቢዎችን እንዳልመረጠ ለማረጋገጥ ተችሏል።

በዚህም መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ ሚያዝያ 5 ቀን 2000 ዓ/ም በልዩ ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች ተዘዋውረው የተመለከቱ የዓይን እማኞች እንደገለፁልን በወረዳ 6 በቀበሌ 08፣09፣11 እና 12 ምርጫ ጣቢያዎች ተመዝግቦ የምርጫ ካርድ ከወሰደው የከተማ ነዋሪ መካከል በጣም ጥቂት ሰዎች በምርጫው ዕለት የተገኙ ሲሆን፣ከመካከላቸውም አብዛኞቹ በድምፅ መስጫ ክፍል “ ሥልጣን ለሕዝብ ልቀቁ! ተቃዋሚ ሳይኖር ብቻችሁን በትዕዛዝ የምትሰበስቡት ድምፅ ሕጋዊ አይሆንም! እናንት ወያኔዎች ለፍርድ የምትቀርቡበበት ወቅት ሩቅ አይሆንም!” የሚሉትንና በፅሑፍ ለመቅረፅ የሚቀፍፉ በርካታ ስድቦችን አስቀምጠው እንደወጡ ለማወቅ ተችሏል።

እንዲሁም በወረዳ 17 በቀበሌ 13፣14፣15 እና 16 በተቋቋሙ ምርጫ ጣቢያዎች ቀኑን ሙሉ መራጭ ስላልመጣ የምርጫ አስፈጻሚዎችና ታዛቢዎች በግል ጨዋታቸው ተመስጠው የዋሉ ሲሆን የወያኔ አገልጋዮች ወደ ማታ ጊዜ ተዘዋውረው በድምፅ ማጉያ ባሰሙት ቅስቀሳ ጥቂት ድምፅ ሰጪዎችን እንዳገኙ ታውቋል።

በተመሳሳይ መልኩ በጎንደር፣በባሕር ዳር፣በሰሜን ወሎና በምሥራቅ ጎጃም የወያኔ የማስመሰል ምርጫ እንዳልተሳካ ከየሥፍራው የደረሱን መረጃዎች ያመለከቱ ሲሆን፣ በተያያዘ ሁኔታ በሐረር እንዲሁም በድሬዳዋ ምርጫው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለወያኔ ያለውን ጥላቻ በከረረ አቋም ያሳየበት እንደ ነበር ለማወቅ ተችሏል።

ሚያዝያ 12 ቀን 2000 ዓ/ም በተካሔደው ምርጫ በተለይ ከጥቂት ካድሬዎችና ከገዥው ጎሣ አባላት በስተቀር ሌሎች ሁሉ በምርጫው ያልተሳተፉ በመሆኑ የምርጫው ሒደት እጅግ ተዝቅዞ ታይቷል።

## ከአንዳንድ ምርጫ ጣቢያ
## የተገኙ የምርጫ ውጤቶች

## ወረዳ 4 ጣቢያ 26/7

| ተ.ቁ | የፖርቲው ስም | ምልክት | ያገኘው ውጤት | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ኢሕአዴግ | ችቦ | 180 | 1ኛ |
| 2 | ቅንጅት | የተጨ. እጆች | 20 | 2ኛ |
| 3 | መኢብን | አምሥት ጣት | 7 | 3ኛ |
| 4 | ኢዴህ | ጋሻና ጦር | 4 | 4ኛ |

## ወረዳ 4

## ጣቢያ 26/27

| ተ.ቁ | የዕጩ ስም | የወከለው ፖርቲ | ምልክት | ያገኘው ውጤት | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወልደ ማሪያም ሀ/ወልድ | ኢሕአዴግ | ችቦ | 175 | 1ኛ |
| 2 | ታደለ በቀለ ገ/ጊዮርጊስ | ቅንጅት | የተጨ.እጆች | 26 | 2ኛ |
| 3 | እንዳለ ኃይሉ ተሰማ | ኢዴአፖ | ሁለት ጣት | 13 | 3ኛ |
| 4 | ሲ/የሺ ነጋሽ ሹራሞ | ኦብኮ | ጀበና | 4 | 4ኛ |
| 5 | ፈንቅሎ በዛብህ ዳዳ | ኢዴፖ | ጦርና ጋሻ | 3 | 5ኛ |
| 6 | ሙሉ ገ/ኪዳን ገ/ሥላሴ | መኢብን | አምስት ጣት | -- | -- |
| 7 | ይማም መአ አህመድ | በግል | ዓሣ | -- | -- |

## አራዳ

## የምርጫ ጣቢያ 05/2

| ተ.ቁ | የዕጩ ስም | የወከለው ፖርቲ | ምልክት | የተገኘው ውጤት | ደረጃ | አሸነn ወይስ አላሸነnም? |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ብሩክታዊት በየነ | ኢ.ሕአዴግ | ችቦ | 405 | 1ኛ | ያሸነn |
| 2 | ግርማ መንግሥቱ | ኢ.ሕአዴግ | ችቦ | 402 | 2ኛ | ያሸነn |
| 3 | ሀርያ ታረቀኝ | ኢ.ሕአዴግ | ችቦ | 402 | 2ኛ | ያሸነn |
| 4 | ክሩቤል አበበ | ኢ.ሕአዴግ | ችቦ | 402 | 2ኛ | ያሸነn |
| 5 | ብዙነሽ በቀለ | ኢ.ሕአዴግ | ችቦ | 402 | 2ኛ | ያሸነn |
| 6 | ተካ አብርሃ | ኢ.ሕአዴግ | ችቦ | 402 | 2ኛ | ያሸነn |
| 7 | ሞገስ ተ/ሚካኤል | ኢ.ሕአዴግ | ችቦ | 402 | 2ኛ | ያሸነn |
| 8 | ለማ ኡልማ | ኢ.ሕአዴግ | ችቦ | 401 | 3ኛ | ያሸነn |

ምንም እንኳን ወያኔ በመላው ኢትዮጵያ ማሸነበን በእጁ በሚገኘው መገናኛ ብዙሃን በተከታታይ ቢለፈልፍም በየጣቢያው ተመዝግቦ የምርጫ ካርድ ከወሰደው አንድ ሺህ ሕዝብ መካከል አብዛኛው ለማንም ድምፅ እንዳልሰጠ ከሰንጠረዦቹ በቀላሉ ለመረዳት ተችሏል።